# ዘ ቅ ዷ ል

የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (ዐኅኢአድ) ልሣን

ዐማራን ከፊጽሞ ጥፋት እንታደግ! ዐኅኢአድ

የዐማራ ኅልውና መጠበቅ፣ ለኢትዮጵያ አንድነት መጠበቅ ዋስትና ነው!

ፈለገ አሥራት የትውልዳችን ቃል ኪዳን ነው!

ልዩ | ዕትም ፲፰ | ቀን መጋቢት ፳፬/፲ | በየ15ቱ ቀን ዘወትር ኀሙስ የሚወጣ




## የሕዝቡ ጥያቄ መሰረታዊ ለውጥ ነው፡፡

የሰሞኑ የኢትዮጵያ ፖለቲካና ፖለቲከኞች የመወያያ ርዕስ የዶ/ር ዐቢይ አሕመድ የትግሬ-ወያኔው ጭምብል «ኢሕዴግ» ሊቀመንበር መሆንና፣ አይቀሬው የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስቴር የመሆን ጉዳይ ነው፡፡ በተወሰነ የሀገራችን ሕዝብ ዘንድ የማይጨበጥ ተስፋ ማጫሩም የሚታይ ነው፡፡ ይሁንና ግን የዶ/ዐብይ ወደ ሥልጣን መምጣት መታየት ያለበት ኢሕአዲግ ከገባበት ማጥ ውስጥ ቢያወጣኝ ብሎ ያደረገው ውስጠ ሹም ሽር አንፃር ነው፡፡ ይህ ውስጠ ሹም ሽር ይበልጥ የሚያተኩረው ኢሕአዲግን ከማጡ ውስጥ ለማውጣት ድርጅታዊ የጥገና ለውጥን ማካሄድ ላይ ይሆናል፡፡ ይህንን ለማድረግ ከዚህ በፊት ድርጅቱ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የጣላቸውን የአፋኝ ድንጋጌዎችን ሊያነሳ ይችላል፡፡ እራሱን ያደሰ አስመስለው ሊያሳዩት ይችላሉ ብሎ የሚያስባቸውን የመቀባባት እርምጃዎችን ሊያደርግ ይችላል፡፡ ከነዚህም ወስጥ ያለጥፋታቸው ያሠራቸውን መፍታት፣ ወታደሩ ከግድያው እንዲታቀብ የማድረግ፣ ለወጣቱ የተወሰነ ጊዜያዊ የሥራ ፈጠራ የማድረግ፣ እሱ በፈጠራቸው የጎሳ ግጭት የተፈናቀሉትን ወደ ቀያቸው የመመለስ ወዘተ ተግባሮችን ሊያካሄድ ይችላል፡፡ ይሁንና እነዚህ መለስተኛ የሆኑ የጥገና መሰል ለውጦች ድርጂቱ ባለፉት 27 ዓመታት የፈጸማቸው ወንጀሎች ናቸው፡፡ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ መልካም ሥራ ተቆጥረው የሚሰጡት ከቶም ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ሕዝቡ በወሰደው ትግሉ በግዴታ እራሱን ተመልሶ እንዲፈትሽ መደረጉ ነው እውነቱ፡፡ ይህ መቀባባት ሕዝቡ ከሚጠይቀው መሠረታዊ ለውጥ ጋር ምንም የሚያገናኛቸው ነገር የለም፡፡

ኢሕአዲግ መለስም መራው ዐብይ ድርጅታዊ ቁመናውና የሚከተለው ረዕዮተ ዓለም ዲሞክራሲያዊ እርምጃን እንዲወስድ አይፈቅድለትም፡፡ከላይ ወደታች በማዕከላዊ ዕዝ የተገነባ ወታደር መሰል ድርጅት ነው፡፡ በድርጅቱ ውስጥ የግለሰቦች ነፃነትና የፈጠራ ችሎታና ሚና ቦታ የላቸውም፡፡

# የሕዝቡ ጥያቄ መሰረታዊ ለውጥ ነው።

በነዚህ ድርጅቶች የውስጥ አሠራረትም ሆነ፣ በግለሰቦች ላይ የመወሰን ሙሉ ሙብትና ሥልጣን ያለው ሁሉንም የመለመላቸውና ያደራጃቸው ሕወሓት ነው። የግለሰቦችም ቦታና ሚና የሚወሰን በድርጅት ውሳኔ ነው። ኢሕአዲግ የኮሚኒስት ድርጅት በካፒታሊዝም ጭንብል ውስጥ ያለ ድርጅት መሆኑ ግንዛቤ ሊያገኝ ይገባል። ዐብይን ማየት ያለብን በኢሕአዲግ ውስጥ ያደገ፣ የተማረና ለሹመት የበቃ ማደጎው መሆኑን ነው። በርግጥ ድርጅቱ በመጥፈያው ወቅት ውስጥ በመግባቱና በተለይም ከመለስ ሞት በኋላ አመራር የለሽ ሆኖ መቆየቱ፣ በወያኔ ጥርነፋ ውስጥ ለነበሩት የኢሕአዲግ አባል ድርጅቶች፣ በድርጅቱ ውስጥ ዕኩልነትን ለማግኘት አጋጣሚው ተፈጥሯል። ዐብይ የሚመጣበት የኦሕዴድ የዕኩልነት ጥያቄም መልስ የሚያገኝበት ጊዜም ዛሬ ሆኗል። በመሁኑም ለዐብይ ሁለት የቤት ሥራዎች ቀርበውለታል። የመጀመሪያው በኢሕአዲግ ውስጥ የቆየውን የሕወሓትን የበላይነት አስተንፍሶ ፣ በመካከላቸው ዕኩልነትን መፍጠር ነው። ሌላው ሥራው የኢሕአዲግን የወንጀል ገጽታውን በማሰማመር ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ ስጦታ ያንን አሳምሮ በማቅረብ የኢሕአዲግን የውድቀት ጊዜን ማራዝም ነው። ይህ ጎዳና ባጭር ጊዜ ውስጥ የዐብይንን ማንነት ፍንትው አድርገው የሚያሳዩ ይሆናሉ። የሕልም ተስፋ የጫረባቸው ዜጎችም ወደ እውነተኛው የትግል ዓለም ይመለሳሉ።

ዐቢይ መጪውን አስፈሪ ጊዜ የሚገነዘብ ከሆነ፣ ድርጅቱንም ከመጥፋት፣ ሀገራችንንም ከማያስፈልግ አደጋ ለመታደግ የሚያስችል አመለካከት ባለቤት ከሆነ፣ ሌላ አማራጭ ጎዳናን ሊከተል እንደሚችል የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ሊጠቁመው ይወዳል። የሚከተለው ጎዳና መልካሙ አማራጭ ነው። የሚወደውን ኢሕአዲግን ለማሻሻል የሚያደርገውን ዘመቻ ይግፋበት። ይህም መሻሻል ማካተት ያለበት በድርጅቱ ውስጥ ያሉ በዘር ፍጅት ፣ በሀገር ክህደት ወንጀል፣በጦር ወንጀል፥ በሕዝብ ሀብት ዘረፋ፣ በሙስናና በቅሚያ የሚጠየቁ አባላቱን የማጥራት እርምጃ፤ ድርጅቱ ወደ ሀገራዊ ድርጅትነት ሊያደርግ ለሚገባ ጉዞው የሚረዱት ተግባሮች ይሆናሉ። ይህንን ውስጠ መሻሻል ካደረገ ፣በሀገሪቱ ውስጥ ካሉ የተቃዋሚ ድርጅቶች ጋር በጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጦ፣ በሀገር የወደፊት ዕጣ ፈነታ ላይ ለመነጋገር ያስችለዋል። በሕዝባዊ የሽግግር መንግሥት አመሠራረት ላይም የማይናቅ ሚና ሊጫወት ይችላል። ዐቢይ ይህንን ጎዞ ከተከተለ፣ ያለምንም ጥርጥር የጥገናዊ ለውጥ ፈታውራሪ ሳይሆን፣ የመሠረታዊ ለውጥ አጋርነቱን አወጀ ማለት ይሆናል። ይህንን ዘመቻ እያደረገ፣ እሱን ገፍቶ ካላበት የሥልጣን ማማ ላይ ያወጣውን የሕዝብ ትግል ሳይቋረጥ የመቀጠሉን አይቀሬነት ለሱ የውስጥ ትግል እንደአጋር አድርጎ ሊቆጥረው ይገባል። በሂደትም በሀገሪቱ ዕጣ ፈንታ ያገባናል ለሚሉት ሁሉ ለሽግግር መንግሥት ምሥረታ ዕውን መሆን እንዲሰባሰቡ ጥሪ ሊያደርግ የግድ ይላል።እነዚህ ሁለት መሠረታዊ የሆኑ ድርጊቶች ዕውን ሲሆኑ ብቻ ነው የዐማራን ሕዝብ ጥያቄን ለመመለስ ከጎዳናው ውስጥ ገብተናል የምንል። ከዚያ መለስ ያለ መቀባባት ኢሕአዲግን ከማይቀርው ውድመቱ ለማዳን የሚደረግ ያልሞት ባይ ተጋዳይ መፍጨርጨር ይሆናል።

ይሁንና ዐቢይ አሕመድ ኮትኩቶ ካሳደገው እና አሁን ለደረሰበት ደረጃ ላበቃው የትግሬ ወያኔ ዓላማና ፍላጎት ተፃራሪ ሆኖ ይቆማል ማለት «ገለባ ያብባል» ከማለት የዘለለ አይሆንም። ከወያኔ ፍልጎት ውጭ ሊንቀሳቀስ የማይችል መሆኑ ማሳያው፣ ኃላፊነቱን የሰጠው ወያኔ፣የራሱ ሰው መሆኑን በሚገባ አጥንቶና አምኖ ከመሆኑም ባሻገር፣ ሕገመንግሥቱ የሚፈቅድለትን፣የራሱን የካቢኔ አባላት እንኳ መምረጥ እንደማይችልና ኢሕአዴግ መርጦ የሰጠውን ብቻ እንደሚቀበል አምኖና ተማምኖ እንደሆነ ግልጽ ነው።

# የሕዝቡ ጥያቄ መሰረታዊ ለውጥ ነው።

ይህም ዐቢይ ሕገመንግሥቱ የሰጠውን ሥልጣንና ኃላፊነት፣ ልክ መለስ ያደርግ እንደነበረው የማድረግ መብቱን ከመጀመሪያው ተገፏል ማለት ነው።

ዐቢይ ሥልጣኑን እንደተረከበ፣ ቢያንስ በራሱ ውሳኔ የራሱን አዲስ ካቢኔ ካላቋቋመ፣ የራሱን ፀሐፊ፣ ጠባቂዎች እና ረዳቶች ካልመረጠና ካልሾመ፣ የአስቸኳይ አዋጁን ካላነሳ፣ የታሰሩትን ሰዎች ካላንዳች ቅድመ ሁኔታ ካልፈታ፣ማናቸውንም የኢትዮጵያ ፖለቲካ ድርጅቶችና በአገራችን ያገባናል የሚሉ ወገኖችን ያላገለለ፣ አስቸኳይ አገራዊ መግባባትና የሽግግር መንግሥት ምሥረታ የሚያመራ የእንተባበርና የአንድነት ጥሪ ካላቀረበ፣ዐቢይ የኃይለማርያም ደሣለኝን ቦታ የወሰደ ሌላው የድርጅቱ ማደጎ ዐቢይ ማለት ነው። ራሱን ካልሆነና፣ የሕልም ተስፋውን ለጣለበት ደጋፊው በትንሹ እንኳ በሕገመንግሥቱ የተሰጡትን የጠቅላይ ሚኒስቴርነት ኃላፊነቶች ለመወጣት ካልጣረ፣እስካሁን የዘመራቸው የኢትዮጵያዊነትና የአንድነን መዝሙሮች፣ ወያኔ አንጋሎ የጋተው የጊዜ መግዣና ጠላቶቼ ናቸው ብሎ የፈረጃቸውን ግለሰቦችና ቡድኖች አድኖ ማስጠፊያ ፣የተጋጋለ የሕዝባዊ እንቅስቃሴ ማዳፈኛ መሣሪያ ሮቦት እንደሆነ ማሳያ ነው። ይህን ለማረጋገጥ ደግሞ ብዙ ጊዜ አይፈጅም። ኃላፊነቱን በተረከበ ማግሥት የምናውቀው ጉዳይ ነው።

ከዐቢይ መሠረታዊ ለውጥ የሚጠበቅ አይደለም። ይህን ለማድረግ የመጣበት መንገድና ለዚህ ኃላፊነት ያበቃው አደረጃጀት አይፈቅድም። ዐቢይ ብዙ የተዘመረለትን ያህል ሆኖ ለመገኘት ማድረግ የሚችለው፣ ሥርዓቱን ተከራክሮ ማሸነፍ የሚያስችለው፣ ሕዝቡንም ከጎኑ ማሰለፍ የሚረዳው የትግሬ-ወያኔ፣ ታግየ፣ «ለብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች» ዕኩልነት ማረጋገጫ የሆነ ሕገመንግሥት በሕዝብ አጸድቄአለሁ እያለ የሚመካበትን መነሻና መድረሻ አድርጎ፣ ሕጉ በሚሰጠው ሥልጣን ተጠቅሞ፣ ከፍ ሲል ከተጠቀሱት በተጨማሪ፣በግፍ የተፈናቀሉ ዐማራ፣ ኦሮሞ፣ ሱማሌና አኙዋኮችን ወደ ነበሩበት ቦታ ከተመጣጣኝ ካሳ ጋር እንዲመለሱ ካደረገ፣ የዘር ማጥፋትና የዘር ማጽዳት ወንጀል የፈጸሙ ግለሰቦችና ቡድኖችን ለፍትሕ የሚያቀርብ ኮሚሽን እንዲቋቋም ያደረገ እንደሆነ፣ የዘመረው ኢትዮጵያዊነትና አንድነት ከመስቀልኛ መንገድ ለማውጣት አንድ እርምጃ ወደፊት እንደተራመደ ሊታይለት ይችላል።

ሕዝባችን ላለፉት 27 ዓመታ የታገለው ለመሠረታዊ ለውጥ ነው። የመሠረታዊ ለውጡም መገለጫው፣ የትግሬ-ወያኔ የዘረጋውን በዘር ላይ የተመሠረተ ሥርዓት አፍርሶ፣በምትኩ የኢትዮጵያ ሕዝብ የመከረበትና ፍላጎቱን የገለጸመት ፣የሕዝቡ የዜግነት መብቱና የግለሰብ ነፃነቱ የተረጋገጠባት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ማየት ነው። በቋንቋ ልዩነት ላይ የተመሠረተው ፌዴሬሽን መሰል አሃዳዊነት የመንግሥት አደረጃጀት ተለውጦ፣ሕዝቡ ለአንድነታችን፣ ለአብሮነታችን፣ ለሰላማችንና ለዕድገታችን ይበጀናል ብሎ በድምፁ ያጸደቀው የመንግሥት አደረጃጀትና የዚሁ ማስፈጸሚያ የሆነ ሕገመንግሥት ባለቤት ሲሆን ነው። የዘመናት ማንነቱ መታወቂያና የነጩ ዓለም የአይደፈሬነት ምልክት የሆነችው አረንጓዴ፣ ብጫና ቀይ ሰንደቅ ዓለላማችን የክብር ቦታዋን ስትይዝና በዓለም አደባባይ አየር ላይ መውለብለብ ስትችል ነው። ለነዚህ ሁሉ መሟላት ሕዝቡ በተወካዮቹ አማካኝነት የሚመክርበትና የሚወስንበት የሽግግር ሥርዓት ሲመቻች ነው። እነዚህ ሁኔታዎች ሲሟሉ የሕዝቡ መሠረታዊ የለውጥ ጥያቄ ደረጃ በደረጃ እየተሟላ መሄዱን ለማየት እንችላለን።

የዐማራው ነገድና የዐማራው ፖለቲከኞችና አክቲቪስቶች በዐቢይ መመረጥ የዐማራው የጎልውና ችግር መፍትሔ ያገኛል ብለው ያምናሉ፣ በዚህም ከትግላቸው ይዘናጋሉ ለማለት አይቻልም።

# የሕዝቡ ጥያቄ መሰረታዊ ለውጥ ነው።

የዐቢይ በዐማራው ላይ የዘር ማጥፋትና የዘር ማጽዳት ወንጀል እንዲፈጸም ፕሮግራም ቀርጾ የተንቀሳቀሰው ሥርዓት ዋና አስፈጻሚ ሆኖ የቆመ እንደመሆኑ፣ ለዐማራው የኅልውና ጥያቄ ይቆማል አይባልም። በዚህም የተነሳ ዐቢይ ተመረጠ ከተባለበት ሰዓት ጀምሮ የተቃውሞ ድምፅ እየተሰማ ያለው፣ ያው ወያኔና እህት ድርጅቶቹ በአውራ ጠላትነት የፈረጁት በዐማራው ልጆች አካባቢ ነው። የዚህ ተቃውሞ መቀጠል ዋና ምክንያቱም፣ አንደኛ የዐማራውን የማንነት ጥያቄ የዐቢይ መመረጥ ሁነኛ መልስ ያስገኝለታል ተብሎ አለመታመኑ ሲሆን፣ ሁለተኛው ምክንያት በሕዝቡ ተቃውሞና በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ግፊት ከእስር ለቀኳቸው ያላቸውን ከሌሎች ነገድ ልጆች ነጥሎ መልሶ ማሰሩና ሌሎችን የዐማራ ወጣት ንቁ ልጆች በገፍ እያሰረ ማሰቃየቱን በማብዛቱ ነው። ይህም በመሆኑ የተዋቅሞው ድምፅ ቀጥሏል። መቀጠልም የግድ ነው።

**የዐማራው የኅልውና ጥያቄ የተሟላ መልስ የሚያገኘው በዐማራው ሕዝብ ትግል ነው።የኃይለማርያም በዐቢይ መተካት፣ የሕዝቡ የተቃውሞ ትግል ያስገኘው መሆኑ ዕውነት ነው። ሕዝባዊ እንቅስቃሴው የወያኔን ፖለቲካዊ መርሕ ከማናጋት አልፎ፣ የስለላና የአፈና መዋቅሩን ከሥር መሠረቱ አናግቶታል። ከስለላ መዋቅሩ መናጋት በተጨማሪ፣ የወያኔ ባሕር የሆነው የትግራይን ሕዝብ ማዕበል ሆኖ እያናወጠው ነው። የትግሬ ሕዝብ እንደ ትናንቱ የወያኔ ቱባ ባለሥልጣኖች አድርግ ያሉትን ለማድረግ ፈቃደኛ አልሆነም። ለምን? እንዴ? ከሁሉም ጋር ደም አቃብታችሁ የት ልታስገቡን አስባችኋል? የሚሉ ጥያቄዎችን እያቀረበ ፊት ለፊት እየተጋፈጣቸው ነው። ይህም የሕዝቡ አመጽ የመግፋት ውጤት ነው።**

*ዐማራው መብቱንና ነፃነቱን የሚያረጋግጠው፣ በስጦታ፣ ወይም በችሮታ ከዐቢይ በሚቸር ቁርስራሽ መብት ሳይሆን፣ በራሱ ልጆች ትግል የሚያገኘው ተፈጥሮአዊ መብቱ ነው። ስለሆነም የዐማራው ተጋድሎ እንቅስቃሴ ኃይሎች፣ በዐማራ ስም የተደራጁ የፖለቲካ፣ የሲቪክ፣ የሙያና የዐማራ ማኅበራት ስብስቦች ኃይላቸውን አጠናክረውና አቀናጅተው በትግሬ-ወያኔ አገዛዝ ላይ ሁለንተናዊ ጫናቸውን ማሳደር ይጠበቅባቸዋል። አቅማዳ፣ቀልቀሎ፣ ቀልቀሎ አቅማዳ ነውና፣ የኃይለማርያም በዐቢይ መተካት የሕዝባችን መሠረታዊ የለውጥ ጥያቄ መመለስ አይችልምና ሳናዘናጋ የዐማራው ወገናችን አንግቦት ለተነሳው የማንነትና የኅልውና ጥያቄ አእምሮአችን ሰብሰብ፤ ኀሊናችን ቆጣ፣ አንድነታችን ጠበቅ፣ ጽናታችን በርታ፣ በማድረግ ለትግሉ አስፈላጊውን መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ እንድንሆን የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ጥሪውን ያቀርባል።*

የዐማራ ኅልውና መጠበቅ ፣ለኢትዮጵያ አንድነት ዋስትና ነው!